Diploma Programme
Programme du diplôme
Programa del Diploma

# Amharic A: literature – Higher level – Paper 1
# Amharique A : littérature – Niveau supérieur – Épreuve 1
# Amhárico A: literatura – Nivel superior – Prueba 1

Friday 8 May 2015 (afternoon)
Vendredi 8 mai 2015 (après-midi)
Viernes 8 de mayo de 2015 (tarde)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

**Instructions to candidates**

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Write a literary commentary on one passage only.
- The maximum mark for this examination paper is **[20 marks]**.

**Instructions destinées aux candidats**

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Rédigez un commentaire littéraire sur un seul des passages.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d'examen est de **[20 points]**.

**Instrucciones para los alumnos**

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Escriba un comentario literario sobre un solo pasaje.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es **[20 puntos]**.



2215 – 0009
© International Baccalaureate Organization 2015

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

ከሚከተሉት ምንባቦች **አንዱን** መርጠህ ስነጽሁፋዊ አስተያየት ስጥ(ስጭ)።

**1.**

ፀጥዋ ለብዙ ሰኮንዶች ሰፈነ። በዚህ መኻል ሰጤ ከመቀመጫው አፈፍ ብሎ በመነሳት ዙሪያውን ወደተሰበሰበው ሰው አስተዋለ። ቀጠለናም፤ “በሉ ተናገሩዪ” አለ።

ድረስ አሞኘ ቁጢጥ ካለበት የኂሊስ ያህል ተፈናጥሮ ተነሳና ኩታውን ማስተካከል ያዘ። የሁሉም ዓይኖች ወደ እሱ ዞሩ። አጭርና ፈርጣማ ነው። አረንጓዴ ቁምጣ፣ ሱሪና ኮት ለብሷል።

“እንግዴህማ ተናገሩ ቻላችሁን ምን ገዶን … ኧረ ተቸግረናል! ልጆቻችን፣ ሚሽቶቻችን ኽዱር ዋሉብን! የትነው ምቴዱ ቲባሉ፣ ታብየ ብዙነህ ዘንድ! የት ነው፤ ታብየ ብዘነህ! … እሳቸውም ተዴ ጃፋቸው ዲያስ ጥለው ሙላውን ሴት ተታዛቸው ስር ኮልኩለው ሲያዩት ነው ሚውሉት አሉ! … እንዴ! ምን ያስፈግጋል! …” የሚስቀውን ተሰብሳቢ በቁጣ ገላመጠው። ዓይኑ ያስፈራል። በድልህ ተለውሶ የተሰራ ነው የሚመስለው።

“በቃ ጠጥታ! ዝም በሉ! … ስማችሁ ተተደረደረው መኻል አንድኛችሁ ጨምሩና ተናገሩ።” ዋና ፀሃፊው ነበር።

“ሰጥ አርጌ ነኝ፣” አሉ አንድ ከዕድሜያቸው ገፋ ያደረጉ አርሶ አደር። አፈር የመሰለ ጋቢ ለብሰ ዋል። ነጭ ክብሳት ራሳቸው ላይ ቂብ ብሏል። “ዛዲያ ብሶብንዪ ምን እናድርግ! … እሱ ነው እንግ ዴህ እንዴህ ሚሰራን! …”

“ማን ነው? በስም ጥራዪ!” ዋና ፀሃፊው ጠየቀ።

“እንዴ! ሙላው ሚያውቀውን፤ … ብዙነህ ነውዪ ዛዲያ ማን ሊሆን፤ እሱ ነው እንዴህ ሚያደርግ! ሴቱን መረን ቢለቅብን ነውዪ፤ ወይ ነዶ ባካችሁ፤ …መቼም ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅ። ሴት ሁላ ማቲውም ጭምር ቲነጋ የሮጠ ወደሱ ቤት ነው፤ እየተስተማርን ነው ይላሉ። ዴርሶም ትምህርት! ኧረ!”

“ምን ይሄ ብቻ!” አለ ድንገት፣ ቢያዝን አሞኘ፣ ድምፁን ከፍ አድርጎ። ምንሽር ጠመንጃ በቀኝ ትከ ሻው ላይ አንግቷል። ከቁምጣ ሱሪው በታች ያሉት ጭኖቹ ያንዳንዳቸው የሙሉ ሰው ወገብ ያክ ላሉ። “… ሴቶች ሁል ጊዜ ራሳችሁን ዝቅ አታዲርጉ! ተወንዶች የበታች ምትሆኑ ለምንዲን ነው? ጃችሁን አትስጡ! እየተባሉ ነው ሚማሩ። ይሄ ነው ትምህርት! …” እንደ ፉከራ እየተንጎራደደ ነበር የሚናገረው። የተሰበሰበው ሰው በተቃውሞ ዓይነት አልጎመጎመ።

“ተንግዴህ የተነገረው ይበቃ ይመስለኛል። ለጥቆ ተራው የአብየ ብዙነህ ነው፣” አለና ዋና ፀሐፊው ሽመላቸውን ተደግፈው ወደ ቆሙት አዛውንት ተመለከተ።

አብየ ብዙነህ በጭራቸው ዓየሩን እየገረፉ፣ እንዲህ አሉ። “ወይ እናንተው! የሽንኅ ዓይን ጉልበት ይሰ ብራል ሲባል ሰምተው ነውኮ እኔን የረቱ መስሏቸው ተጀማው ፊት ያቆሙኝ። ሳይዴግስ አይጣ ላም። ይኸው ለኔም ሆነልኝ። አሁን ይሄን ሁሉ ወገን እንዲህ ባንዲጋ ሁኖ ተየት አገኘው ነበር! ጉድ ኮ ነው እናንተ! ሴት ወገናችን አይደለችም ነው ምትሉ? ሁላችንስ ብንሆን በእናታችን በእምዬ፣ በህቶቻችን በእነኡታለም፣ በልጆቻችን በእነአንጓቹ ሴትም አዶለን! ሴት የጌታ እናትም አዶለች ወይ! በሉስቲ ተናገሩ!” በጭራቸው ዓይሩን እየቀዘፉ ዙሪያውን ተመለከቱ። አንዳንዱ ከንፈሩን ይመጣል።

“ሴት ትውዴቅ፣ ተኛ እግር በታች ትሁን ነው ምትሉ? ሴትን የውሻችንን ያህል እንኳ ክብር የምንነፍጋት እኛ ምንዲን ነን? ለምንዲን ነው ይሄን ምናዴርግ? …ለምን? ምንስ በወጣት! እኛን ስላገለገለች! ለኛ ትትል ስለምትዴክም! …እሷስ ጥሎባተዪ ዴስ ይላት መሰላችሁ! …ቻረ ተው ግዴለም ልብ እንግዛ! …እስቲ ያሰሴት ምን የሚሆንልን ነገር ይኖራል? ተምኝታችን ተነስተን ሰማይና ምዲር እስቲሳሳም ያሰሴት ምናዴርገው ነገር አለን? ብናርስ፣ ብንዘራ፣ ብናጭዲና ብንወቃ ማብቂያው በሴ ትም አዴል! እስከመቼ ነው በሴት ላይ ጡር ምንውል? ሴትና ወንፊት ማይችሉት የለም እያልን ጡዋትና ማታ እነሱኑ መጫንን፣ መፈርጠቅንና ማከላተምን ሳንተው ነው?”

ሀይለ ገብርኤል እንደሻው፣ *ያላደፉ ነፍሶች እና ሌሎች*፣ (2013)።

**2.**

አንበሳውን ልሁን ጡንቻዬን ላፈርጥም፤
እንዳደቅቀው በክርን ይህንንም፤ ያንንም፤
    እባቡን ልሁነው፤ ልቤን እግር ላርገው
    ሰርስሬ፤ መርዤ፤ ደሙን እንድጠጣው፤
ምስጥ ልሁንና ሬሣውን ልብላ፤
የሞተው ሞልቶኝ ከአለው አልጣላ፤
    እስስቲቱን ልሁን ከሁሉም ልዳራ፤
    መስሎ መብላት ሳለ ጠላት ለምን ላፍራ!
ጥንቸልዋን ልሁነው፤ በፍርሃት ልሽቆጥቆጥ፤
ሳገኝ እየበላሁ ሲመጡብኝ ልሩጥ
    ውሻ ልሁንና ይቁላላ ጅራቴ፤
    ግብዙን ላስደስት፤ ይጫወት በእምነቴ፤
አህያውን ልሁን፤ ልደድብ በትዕግስት፤
ይነርቱኝ ይዘው፤ ይጫኑብኝ ኩበት፤
    እውቀት፤ እውነት፤ እምነት፤ ቅንነት፤ ግልጽነት፤
    ዋጋቸው ምን ይሆን? የሰውነቴ ሀብት፤
እውነተኛ ልሁን? ወይስ ልሁን ታማኝ?
የቱ ያኮራኛል? የቱ ነው እሚያበላኝ?
    ለምን ላስብ ቀድሞ? ምንስ ያሰጋኛል?
    ለሆዴ እንደሆነ ሕሊናና አእምሮን መሸጥ ይበቃኛል፤
ልብላ? ልበስብስ በቁሜ? ከብሬ ልከበር?
ወይስ ልሙትና ኮርቼ ልቀበር?
    ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ መሆኑን አውቃለሁ፤
    አልቀበር እንጂ እኔኮ ሞቼአለሁ፤
አላማው ጠፋብኝ፤ ፍጹም ግራ ገባኝ፤
መልአክነት ስመኝ፤ ሰው መሆን ከብዶብኝ፤

*መስፍን ወልደ ማርያም፣ ዛሬም እንጉርጉሮ፣* (2013)::